## በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የታዳሽ ሀይሎች

ጉዳት የሚያስከትሉ የግሪን ሀውስ ጋዞች ልቀት በሌለበት ሁኔታ ከተማዋ ሀይል እንድታገኝ በታዳሽ ሀይሎች ላይ በመደገፍ፤ ዲስትሪክቱ የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ የሚደረገውን ውጊያ ይመራል። የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ አገልግሎት ኮሚሽን (ዲ.ሲ.ፒ.ኤስ.ሲ) እና ሌሎች ድርጅቶች በ2032 ዲስትሪክቱ 100% ከታዳሽ ሀይሎች ሀይል ለማግኘት ያስቀመጠውን ግብ ለማሳካት ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ።

## ቀጣይነት ያለው የሶላር (የጸሐይ ሀይል) እድገት

261 የማህበረሰብ የታዳሽ ሀይል ተቋማትን ጨምሮ ከአፕሪል 22 ጀምሮ በዲስትሪክቱ ውስጥ ከ13,600 በላይ የሶላር ተቋማት ስለመኖራቸው ዲ.ሲ.ፒ.ኤስ.ሲ ያረጋገጠ ሲሆን፤ ሁሉም 205 ሜጋዋት የሚጠጋ ንጹህ ሀይል ያመነጫሉ።

- በአጠቃላይ ድርጅቱ ወደ 30,000 ቤቶች ሀይል እንዲያገኙ የሚያስችሉ በቂ የሶላር ፓነሎች አሉት።
- በጆይንት ቤዝ አንኮሲታ በሊንግ የሚገኘው የሶላር ሀይል ማመንጫ ብቻውን ለ786 የዲሲ ቤቶች የሚበቃ ሀይል ያመነጫል።
- ወደ ኤሌክትሪክ መኪናዎች የሚደረግ ሽግግር
- ቀጣይነት ባለው የሀይል መሰረተ ልማት አቅም ግንባታ እና የህንጻ እና ፓይፕ ላይን ፕሮግራም አማካኝነት የታዳሽ ሀይል እና የሀይል ቁጠባ ኢኒሼቲቮችን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ማጠናከር

**DCPSC.org/CleanEnergy**

## የዲሲ ሀይል ግንኙነት

የሀይል አቅርቦታቸውን በተመለከተ የዲስትሪክቱ የሀይል ሸማቾች ምርጫ አላቸው። የእርስዎ ትኩረት በጊዜ ሂደት የሚኖር ቋሚ ዋጋ፣ የካርቦን አስተዋጽኦዎን መቀነስ ወይም ተጨማሪ አገልግሎቶችን ማግኘት ከሆነ ለቤትዎ የተሻለውን የሀይል አማራጭ መምረጥ ያስፈልግዎታል።

ከ DCPowerConnect.com ላይ የአቅራቢዎችን ዋጋ ያነጻጽሩ።

## ተጨማሪ ንጹህ ሀይል እና የሀይል ቁጠባ ፕሮግራሞች

**ዲ.ሲ.ኤስ.ኢዩ**

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሰስተይነብል ኢነርጂ ዩቲሊቲ (ዲሲኤስኢዩ) እርስዎ ለራስዎ እና ለቤትዎ ትክክለኛውን የሀይል ምርጫ ለማድረግ የሚያስችልዎትን ግብአቶች ያቀርብልዎታል። የፋይናንስ ማበረታቻዎችን፣ ቴክኒካዊ ድጋፎችን እና መረጃዎችን በማቅረብ የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች እና ድርጅቶች አነስተኛ ሀይል እንዲጠቀሙ እና ገንዘብ እንዲቆጥቡ ዲሲኤስኢዩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርግላቸዋል።

## ሶላር ፎር ኦል

የሶላር ፎር ኦል ዓላማ በዲስትሪክቱ ውስጥ ለሚገኙ አነስተኛ ገቢ ያላቸው 100,000 ቤተሰቦች የሶላር ሀይል እንዲያገኙ ማስቻል ነው። የዲሲ የሀይል መስሪያ ቤት እና አካባቢያዊ አጋሮች እንዲሁም በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች በእያንዳንዱ ቤተሰብ ቤት ላይ ሶላር የሚገጥሙ እና በርካታ ቤተሰቦች በሚኖሩባቸው ህንጻዎች ላይ ኪራዮችን እና ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የማህበረሰብ ሶላር ፕሮጀክቶችን ለማጎልበት ይሰራሉ።

## ፔፕኮ ኢነርጂ ዋይዝ ሪዋርድስ

የፔፕኮ ኢነርጂ ዋይዝ ሪዋርድስ ፕሮግራም የዲስትሪክቱ የኤሌክትሪክ ሸማቾች የሀይል አጠቃቀማቸውን የበለጠ መቆጣጠር እንዲችሉ፣ ለሀይል የሚያወጡትን ወጪ እንዲቀንሱ እና እንዲቆጥቡ እንዲሁም የበለጠ ቀጣይነት ያለው የህይወት ዘይቤ ውስጥ ለመግባት እምርታ እንዲያደርጉ የሚያግዛቸው መሳሪያ ነው።